ቅድመ ልጅነት አስተማሪ
ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ

# በበጀት አመት 2025 (FY25) ለመሳተፍ እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ

*ለአዳዲስ አገልግሎት አቅራቢዎች መመሪያዎች*

## ይህንን መመሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል

ይህ መመሪያ በ FY24 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ላልተሳተፉ እና በ FY25 በሚጀመረው ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች መመሪያዎችን ይሰጣል።

በልጅ እንክብክባኤ የድጎማ ፕሮግራም ላይ የሚሳተፉ እና በ FY25 በሚጀምረው የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች የትምህርት አገልግሎቶች ተቆጣጣሪያቸውን ሊያነጋግሩ ይገባል።

በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ላይ የተሳተፉ እና የ FY24 አገልግሎት አቅራቢ ስምምነታቸውን ማራዘም የሚፈልጉ የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች OSSE.ECEPayEquity@dc.govን ሊያነጋግሩ ይገባል።

## ድጋፍ የት ማግኘት እንደሚቻል

ለጥያቄዎች ወይም የማመልከቻ ሂደትን ለማጠናቀቅ፣ ወደ OSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል ይላኩ ወይም ለምናባዊ የስራ ሰአታት ቀጠሮዎች ይመዝገቡ።

## የማመልከቻ ሂደት

በ FY25 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ውስጥ ለመሳተፍ፣ አቅራቢው የሚከተሉት ማድረግ አለበት፡-

1. የ FY25 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ማመልከቻን (*በቅድመ ትምህርት ፈቃድ መስጫ መሰሪያ ክፍል [DELLT]*) ሞልቶ ማስገባት

2. የFY25 ፈቃድ ያለው ተወካይ ቅጽ (*በ Smartsheet*) ሞልቶ ማስገባት

3. የ FY25 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ አቅራቢ ስምምነትን (*በ Adobe Acrobat sign)* ሞልቶ መፈረም።

*ማሳሰቢያ፦ ማመልከቻ እና/ወይም ፈቃድ ያለው የውክልና ቅጽ መሙላት አንድ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ እንደሚሳተፍ ዋስትና አይሰጥም። የገንዘብ ድጋፎችን ለመቀበል አገልግሎት አቅራቢው የአቅራቢ ስምምነቱን ሞልቶ ማስገባት አለበት።*

## ቁልፍ ቀነ ገደቦች

| **የFY25 የማመልከቻ እና የስምምነት ማስረከቢያ ቀነገደቦች**<br>**ሁሉም ቀነ ገደቦች 5 p.m. ላይ ናቸው ET* | | | |
|---|---|---|---|
| **ሩብ ዓመት** | **በ DELLT ማመልከቻ ለመሙላት ቀነ ገደብ** | **የአቅራቢ ስምምነት ለማስፈጸም ቀነ ገደብ** | **የሽልማት ክፍያ ስርጭት** |
| ሩብ አመት አንድ | ሴፕቴምበር 15፣ 2024 | ሴፕቴምበር 30፣ 2024 | ዲሴምበር 2024 |
| ሩብ አመት ሁለት | ዲሴምበር 15፣ 2024 | ዲሴምበር 31፣ 2024 | ማርች 2025 |
| ሩብ አመት ሶስት | ማርች 15፣ 2025 | ማርች 31፣ 2025 | ጁን 2025 |
| ሩብ አመት አራት | ጁን 15፣ 2025 | ጁን 30፣ 2025 | ሴፕቴምበር 2025 |

አንድ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ የFY25 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ስምምነት ከፈጸመ በኋላ (ለምሳሌ ፈርሞ ወደ OSSE ከመለሰ) የፕሮግራሙን መስፈርቶች ማሟላታቸውን እስከቀጠሉ ድረስ የቀረውን የ FY25 ሽልማት ክፍያዎች ወዲያውኑ የሚቀበሉ ይሆናል። አገልግሎት አቅራቢዎች በየሩብ አመቱ አዲስ ማመልከቻ ማስገባት አይጠበቅባቸውም።

የFY25 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ማመልከቻ እስከ እሁድ፣ ጁን 15፣ 2025 5 p.m. ድረስ ክፍት ሆኖ ይቆያል(ለሩብ አመት አራት በDELLT ውስጥ ማመልከቻ ለመሙላት ቀነ ገደብ)። የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች የእያንዳንዱን ሩብ አመት የማመልከቻ እና የስምምነት ቀነ ገደብ ሊያስታውሱ ይገባል። አንድ አገልግሎት አቅራቢ ለዚያ ልዩ ሩብ አመት የሽልማት ክፍያ ለመቀበል ከላይ የታዘዘውን የሩብ አመት ማመልከቻ እና የስምምነት ቀነ ገደብ ማሟላት አለበት።

## የማመልከቻ ማጠቃለያ

በ DELLT ውስጥ አራት የማመልከቻ ክፍሎች አሉ። ማመልከቻውን በጊዜው ለመሙላት፣ አገልግሎት አቅራቢዎች መረጃውን መመልከት እና አስቀድመው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አስፈላጊ ሰነዶች መሰብሰብ እና ማሟላት አለባቸው።

- **የስነ ህዝብ አወቃቀር መረጃን መገምገም እና ማረጋገጥ**
- **ማረጋገጫዎችን ማንበብ እና እውቅና መስጠት**
  - የ2004 የቋንቋ ተደራሽነት ህግ
  - የ2006 የኑሮ ደመወዝ ህግ
  - ይፋ ያልሆነ ስምምነት
- **አስፈላጊ ሰነዶችን ማስገባት**
  - የIRS የአሰሪ መለያ ቁጥር (EIN) የማረጋገጫ ደብዳቤ
    - አቅራቢዎች የEIN ማረጋገጫ ደብዳቤያቸውን ቅጂ ማስገባት አለባቸው።
    - ለስራዎ ከዚህ ቀደም አመልክተው EIN ከተቀበሉ፣ ነገር ግን ያለቦታው ካስቀመጡት፣ ከIRS የስራ እና ልዩ የግብር መስመር በ800-829-4933 ከሰኞ እስከ አርብ ከ7 a.m.–7 p.m በመደወል የእርስዎን EIN መጠየቅ ይችላሉ።
  - የIRS ቅጽ W-9
    - እዚህ የሚገኘውን የIRS ቅጽ W-9 ያውርዱ።
    - ትክክለኛውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለማቅረብ ቅጹን ይሙሉ።
  - የዲስትሪክት የተቀናጀ የፋይናንስ ስርዐት (DIFS) አቅራቢ የፈቃድ ሰነድ
    - በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ለመሳተፍ፣ አገልግሎት አቅራቢው በዲሲ ዋና የፋይናንስ መኮንን ቢሮ (OCFO) በሚተዳደረው የዲስትሪክት መንግስት የፋይናንስ ስርዐት በሆነው በዲስትሪክት የተቀናጀ የፋይናንስ ስርዐት (DIFS) መመዝገብ አለበት።
    - **በ DIFS ውስጥ ለመመዝገብ እነዚህን መመሪያዎች ይከተሉ.**።
    - ስለ DIFS ምዝገባ ጥያቄዎች ካሉ፣ ለOCFO በ suppliers@dc.gov ኢሜይል ይላኩ ወይም ወደ (202) 442-6870 ከሰኞ እስከ አርብ በ8 a.m. እና 5 p.m. መካከል ባለው ሰአት ይደውሉ
    - አገልግሎት አቅራቢው በ DIFS ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ከተመዘገበ በኋላ፣ አገልግሎት አቅራቢው ከ DIFS/OCFO የማጽደቂያ ኢሜይል የሚቀበል ይሆናል። የማጽደቂያ ማሳወቂያ ኢሜይል የPDF ቅጂን ያስቀምጡ። ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ የመርጦ-የመግባት ሂደቱን ለማጠናቀቅ አገልግሎት አቅራቢው የማጽደቂያ ማሳወቂያ ኢሜይሉን የተሳካ የ DIFS አቅራቢ ምዝገባ ማረጋገጫ አድርጎ ለ OSSE ማቅረብ አለበት።
    - ማሳሰቢያ፦ አስቀድመው በDIFS ውስጥ ከተመዘገቡ፣ አዲስ መለያ አይፍጠሩ። በDIFS ውስጥ መመዝገብዎን ማረጋገጫ ለመጠየቅ እባክዎ OCFOን ያነጋግሩ። አስቀድሞ የ DIFS መለያ እንዳለዎት እርግጠኛ ካልሆኑ እባክዎ ከላይ ያለውን የመገኛ መረጃ በመጠቀም OCFOን ያነጋግሩ።
- **በፕሮግራሙ ውስጥ ለመሳተፍ ተቋሙን ወይም ተቋሞቹን ይለዩ**

- ብዙ ተቋማት ላይ የሚሰሩ የልጅ እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢዎች ለእያንዳንዱ ጣቢያ ማመልከቻ መሙላት <u>አይጠበቅባቸውም</u>። በማመልከቻው ውስጥ፣ አገልግሎት አቅራቢው በፕሮግራሙ ውስጥ የሚሳተፉትን ተቋማት ሊያመለክት ይችላል። አገልግሎት አቅራቢዎች በማመልከቻው ወቅት ሁሉንም ብቁ ተቋማት እንዲያካትቱ ይበረታታሉ።

## ለአዳዲስ አገልግሎት አቅራቢዎች ማመልከቻውን በ DELLT ለማጠናቀቅ ደረጃዎች

**ደረጃ 1፡- ወደ DELLT ይግቡ።**

**ደረጃ 2፡- “ፍትሃዊ ክፍያ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።**



ደረጃ 3፥ “በፍትሃዊ ክፍያ ለመሳተፍ ጠቅ ያድርጉ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።




እዚህ ጠቅ ያድርጉ

ደረጃ 4፥ የእርሳስ አዶውን ጠቅ ያድርጉ።




እዚህ ጠቅ ያድርጉ

**ደረጃ 5፥ የስነ ህዝብ አወቃቀር መረጃን ይገምግሙ።**

በስነ ህዝብ ክፍል ውስጥ የቀረበውን መረጃ ይገምግሙ። በዚህ ክፍል ውስጥ ማንኛቸውም ስህተቶች ካሉ፣ እባክዎ የተቋሙን የተመደበ ፈቃድ ሰጪ ልዩ ባለሙያ ያነጋግሩ።


Home

Provider Agreements > Edit Agreement #366

PROVIDER INFORMATION

Demographics

| | |
|---|---|
| **Provider Name**<br>** Test Provider Non Subsidy Role** | **Provider Mailing Address**<br>1050 First Street Northeast, Washington, District of Columbia 20002 |
| **Contact Name**<br>ADT Quickbase | **Ward**<br>3 |
| **Contact Type**<br>Owner/Director | **Quadrant**<br>NW |
| **Provider Phone**<br>(202) 336-7891 | **Assigned PEP**<br>ROBIN WALLACE |
| **Provider Email**<br>adtquickbase4@gmail.com | **PEP Email**<br>Robin.Wallace2@dc.gov |
| **Legal Entity Type**<br>Government Agency | **PEP Phone**<br>(202) 727-8147 |

**ደረጃ 6፥ ማረጋገጫዎችን ይገምግሙ እና ለደረሰኝ እውቅና ይስጡ።**

በማያ ገጹ በግራ በኩል ያሉትን እያንዳንዱን የደመቁ ማስፈንጠሪያዎች ጠቅ ያድርጉ (*የ2006 የኑሮ ደመወዝ ህግ፣ የቋንቋ ተደራሽነት ማረጋገጫ እና ይፋ ያልሆነ ስምምነት ማረጋገጫ ቅጽ*)። እያንዳንዱ ሰነዶች እንደወረደ ፋይል ሆነው የሚታዩ ይሆናል። እያንዳንዱን የማረጋገጫ ሰነዶች ለማግኘት በእርስዎ የወረዱ ሰነዶች ማህደር ውስጥ የሚገኘውን ሰነድ ይምረጡ። እያንዳንዱን የማረጋገጫ ሰነዶች ካነበቡ በኋላ፣ እያንዳንንዱ የማረጋገጫ ሰነዶች መገምገማቸውን ለማረጋገጥ ምልክት ማድረጊያ ሳጥኖቹን ጠቅ ያድርጉ።



**ደረጃ 7፥ ደጋፊ ሰነዶችን ይጫኑ።**

የአገልግሎት አቅራቢውን የIRS EIN ማረጋገጫ ደብዳቤ፣ የ IRS ቅጽ W-9 እና የ DIFS አቅራቢ ምዝገባ ማረጋገጫን ለመጫን "ፋይል ይምረጡ" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።


Supporting Documentation

Upload the completed supporting documentation below

IRS Employer Identification Number (EIN) Confirmation Letter

Choose File No file chosen

IRS Form W-9

Choose File No file chosen

District Integrated Financial System (DIFS) Supplier Approval Documentation

Choose File No file chosen

**ደረጃ 8፦ በፕሮግራሙ ውስጥ የሚሳተፉትን የሚሰሩበትን/ባቸውን ተቋም ወይም ተቋማት ይለዩ**

በ FY25 በፕሮግራሙ ውስጥ እንዲሳተፍ ላሰቡት እያንዳንዱ ተቋም "በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ውስጥ ለመሳተፍ ፍላጎት ያለው" በሚለው ረድፍ ላይ ባለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ።


FACILITY INFORMATION

More ▾ 2 Facility records

| Facility Name | Interested in participating in the Early Childhood Educator Pay Equity Fund |
|---|---|
| ** Test Non Subsidy Role 5 | ☐ |
| ** Test Non Subsidy Role 6 | ☐ |

Notes/Comments

-

| Status | Assigned To | Created by | Created By | Comments/Notes |
|---|---|---|---|---|

No log records found

Submit Save Cancel

**ሳጥኑን ወይም ሳጥኖቹ ላይ ምልክት ያድርጉ**

**ደረጃ 9፡- ማመልከቻውን አስቀምጠው ያስገቡ።**




**ደረጃ 10፡- ማመልከቻ ማስገባትዎን ለ OSSE ያሳውቁ**

ማመልከቻው በ DELLT ውስጥ ማስገባትዎን ለማሳወቅ ወደ OSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል ይላኩ። ከዚያም OSSE መሟላቱን ለማረጋገጥ ማመልከቻውን የሚገመግም ይሆናል። OSSE ማመልከቻው ያልተሟላ መሆኑን ከወሰነ፣ ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ቡድን አንድ አባል የጎደለውን የማመልከቻ ክፍል(ሎች) ለመወያየት የአቅራቢውን ተጠሪ የሚያነጋግር ይሆናል። የተሟሉ ማመልከቻዎችን የሚያቀርቡ አገልግሎት አቅራቢዎች ወደ ማመልከቻው ሂደት ሁለተኛ ምዕራፍ ይሸጋገራሉ፦ ፈቃድ ያለው የውክልና ቅጽ መሙላት።

## ፈቃድ ያለው የውክልና ቅጽ መሙላት

OSSE ፈቃድ ያለውን የውክልና ቅጽ በ DELLT ውስጥ ማመልከቻውን ላሟሉ አገልግሎት አቅራቢዎች በኢሜይል ይልካል። አገልግሎት አቅራቢዎች ቅጹን መሙላት እና በ OSSE በቀረበው የ Smartsheet ማስፈንጠሪያ በኩል ማስገባት አለባቸው።

ፈቃድ ያለው ተወካይ ቅጽን በጊዜው ለመሙላት አገልግሎት አቅራቢዎች ከዚህ በታች ያለውን መረጃ አስቀድመው ሊሰበስቡ ይገባል፦

- EIN
- የሽልማት አስተዳደር ልዩ አካል መታወቂያ (SAM UEI) ቁጥር እና የአገልግሎት ማብቂያ ቀን ስርዓት

- SAM UEI የሌላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች ለአንዱ ለመመዝገብ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉትን ደረጃዎች ሊከተሉ ይገባል።

ፈቃድ ያለው የውክልና ቅጽ በ Smartsheet በኩል ከገባ በኋላ አገልግሎት አቅራቢው ወደ ሶስተኛው እና የመጨረሻው የማመልከቻ ሂደት ምዕራፍ የሚሄድ ይሆናል፦ የ FY25 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ የአገልግሎት አቅራቢ ስምምነትን ማሟላት።

## የአገልግሎት አቅራቢ ስምምነትን ማሟላት

OSSE የ FY25 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ የአገልግሎት አቅራቢ ስምምነትን ፈቃድ ያለውን የውክልና ቅጽ በ Adobe Acrobat Sign ለሞሉ አገልግሎት አቅራቢዎች የሚልክ ይሆናል።

የአገልግሎት አቅራቢውን ስምምነት በጊዜ ለማጠናቀቅ፣ አገልግሎት አቅራቢዎች የ FY25 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ የአገልግሎት አቅራቢ ስምምነት ናሙናን ሊመለከቱ ይገባል። ስለ ስምምነቱ ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉ ወደ OSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል ይላኩ። ስምምነቱን በሚያጠናቅቁበት ጊዜ አገልግሎት አቅራቢዎች የ SAM UEI ቁጥራቸውን እና የአገልግሎት ጊዜው የሚያበቃበትን ቀን እንዲያስገቡ የሚጠየቁ ይሆናል።

## ጥያቄዎች?

ለጥያቄዎች ወይም ማመልከቻውን ለመሙላት ድጋፍ ለማግኘት፣ ወደ OSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል ይላኩ ወይም ለምናባዊ የስራ ሰአታት ቀጠሮዎች ይመዝገቡ።